# የ 2020 - 2021 የትምህርት ዓመት የቅድመ ሙአለህፃናት/ሄድስታርት ፕሮግራሞች የዶኩመንቶች ዝርዝር

Division of Title I and Early Childhood Programs and Services
Rocking Horse Road Center, 4910 Macon Road, Room 143, Rockville, Maryland 20852

ለቅድመ ሙአለህፃናት/ሄድስታርት ልጆች፣ የአካል ስንክልና ያላቸውን ህጻናት ጨምሮ ያለቀጠሮ በአካል ማመልከቻ ቅጽ/ፎርም ይዘው ለመቅረብ ከሰኞ እስከ ዓርብ ከ 9:00 a.m. እስከ 4:00 p.m. በ Rocking Horse Road Center, 4910 Macon Road, Rockville, Maryland, 20852 መቀበል ይቻላል። የቀጠሮ (ሰአቶች) ይኖራሉ። በዚህ ቅጽ ላይ ስለተጠቀሱት ሠነዶች ጥያቄዎች ካሉዎት እና/ወይም የእርስዎን የተለየ ሁኔታ በሚመለከት የበለጠ መረጃ ለማግኘት እባክዎ በስልክ ቁጥር:- 240-740-4530 ይደውሉ ወይም ይህንን ድረ-ገጽ ይጎብኙ:- www.montgomeryschoolsmd.org

**ማመልከቻውን ለመሙላት፣ ከዚህ በታች የተጠቀሱትን ሠነዶች ማቅረብ አለብዎት።**

የሚከተለውን ዝርዝር በመመሪያነት ይጠቀሙ:-

❏ 1. የተማሪ የእድሜ ማረጋገጫ እና መታወቂያ— ከዚህ በታች ከተዘረዘሩት ሠነዶች/ዶኩመንቶች አንዱን ያቅርቡ።
- የልደት ሠርተፊኬት
- ፓስፖርት
- የሃኪም ማስረጃ
- የጥምቀት ወይም የቤተክርስቲያን ሠርተፊኬት
- የሆስፒታል ሠርተፊኬት
- የሠነድ ማረጋገጫ/ኖቶራይዝ የተደረገ የወላጅ ቃለመኃላ/affidavit
- የልደት ምዝገባ ሠርተፊኬት፣ ወይም
- ሌሎች ህጋዊ የሆኑ ወይም የሠነድ ማረጋገጫ ኖቶራይዝ የተደረጉ የልጆች መታወቂያ እና የልደት ቀን ማረጋገጫ።

❏ 2. ተማሪው(ዋ)ን ወደ ትምህርት ቤት የሚያስገባው/የምታስገባው ሰው መታወቂያ እና ከተማሪው(ዋ) ጋር ያለ ግንኙነት—
ፎተግራፍ ያለበት የማንነት መታወቂያ—እባክዎ ከዚህ በታች ከተዘረዘሩት ሠነዶች/ዶኩመንቶች አንዱን ያቅርቡ።
- የመንጃ ፈቃድ
- ፓስፖርት
- ከሞተር ተሽከርካሪ የሚሰጥ መለያ/መታወቂያ ካርድ
- ሌላ ______________________________

ከተማሪ ጋር ያለ ግንኙነትን በሚመለከት የሚከተሉት ሠነዶች—ከዚህ በታች ከተዘረዘሩት ሠነዶች/ዶኩመንቶች አንዱን ያቅርቡ።
- የልጅ የልደት ሠርተፊኬት
- የፍርድ ቤት ትዕዛዝ
- ለመለያየት የተደረገ ስምምነት ወይም የፍቺ ሠነድ፣ ወይም
- ሌላ ህጋዊ መታወቂያ ______________________________

❏ 3. የቤተሰብ የገቢ ማረጋገጫ (ጎልማሳ የቤተሰብ አባላት በሙሉ)— ከዚህ በታች ከተዘረዘሩት ሠነዶች/ዶኩመንቶች እርስዎን የሚመለከቱ ሠነዶችን በሙሉ ያቅርቡ።
ለምሳሌ፡-
- Tax return for 2019—1040, W2s, Schedule C/1099
- ሦስት ወቅታዊ የደሞዝ (ቼጅ) ክፍያ ሠነዶች/pay stubs
- የሥራ ቅጥር ደብዳቤዎች
- ስለ ልጅ ማሳደጊያ ድጋፍ የፍርድ ቤት ትዕዛዝ ወይም ደብዳቤ
- የዶላር መጠን የሚያሳይ የፋይናንስ እርዳታ ደብዳቤ
- የ Temporary Cash Assistance (ጊዜያዊ የጥሬ ገንዘብ ድጎማ)(TCA) ክፍያዎች
- የኪራይ ገቢ ደብዳቤዎች
- የሥራ አጥነት፣ የአካል ስንክልና ገቢ፣ ወዘተ

❏ 4. ወቅታዊ የሞንትጎመሪ ካውንቲ ነዋሪነት ማስረጃ
- የግል መኖሪያ ቤት ባለቤት ከሆኑ—ተቀባይነት የሚኖረው ወቅታዊ የንብረት ታክስ ሠነድ ነው
- በኪራይ ቤት የሚኖሩ ከሆነ—ተቀባይነት የሚኖረው ወቅታዊ ሊዝ ነው* (የሚመለከትዎ ከሆነ፣ የ HOC፣ የኪራይ ወይም ዩቲሊቲ ድጋፍ የሚሰጥ ካለ አባሪ ይደረግ)።
- *ኦርጅናል የሊዝ ስምምነት ያበቃለት ከሆነ፣ የሊዙን ቅጂ እና ወቅታዊ ዩቲሊቲ ቢል ያቅርቡ
- በ MCPS ትምህርት ቤት አካባቢ በህጋዊነት ኗሪ ከሆነ/ች የቤት ባለቤት ጋር ወይም ከተከራይ ጋር በደባልነት የሚኖሩ ከሆነ—
- የሠነድ ማረጋገጫ ማህተም/ኖቶራይዝ የተደረገ MCPS Form 335-74፣የመኖሪያ ቤት ደባልነት መግለጫ/Shared Housing Disclosure በአግባብ ተሞልቶ መቅረብ አለበት፣ የቤት ባለቤትነት ወቅታዊ የንብረት ታክስ ሠነድ/ቢል ቅጂ፣ ወይም የመኖሪያ ቤት ኪራይ-ሊዝ ቅጂ (ኦርጅናል የኪራይ ውል/ሊዝ ጊዜው ያለፈበት ከሆነ፣ የሊዝ ውል ቅጂ እና ዩቲሊቲ ክፍያ ሠነድ-ቢል)፣ ተፈርሞበት ኖቶራይዝ የተደረገ የ MCPS Form 335-74፣ እና ወላጅ/ሞግዚት ወይም ብቁነት ያለው/ያላት ተማሪ በተገለጸው አድራሻ ነዋሪ ስለመሆናቸው የሚያረጋግጥ ሦስት ዶኩሜንቶችን ማቅረብ። MCPS Form 335-74 ተሞልቶ እና ተፈርሞበት ህጋዊ ሰነድ መሆኑን ሲፈረም የተረጋገጠ/notarized ከሆነ አድራሻ ለማረጋገጥ ከሦስቱ አስፈላጊ ማረጋገጫዎች አንዱ ሆኖ ሊቆጠር ይችላል።

❏ 5. እባክዎ የእርስዎን ሁኔታ የሚመለከት ከሆነ የሚከተሉትን ሠነዶች/ዶኩመንቶች ያቅርቡ:-
- የልጁ/ልጅቷ የህክምና ኢንሹራንስ/መድህን (የሚመለከትዎ ከሆነ)
- WIC Folder-ፋይል (የሚመለከትዎት ከሆነ)
- የምግብ ድጎማ ፕሮግራም/Food Supplement Program (FSP) ደብዳቤ (ቀደም ሲል ፉድ ስታምፕስ ይባል ነበር) (የሚመለከትዎ ከሆነ)
- የልጅ እንክብካቤ ድጎማ ቫውቸር (የሚመለከትዎ ከሆነ)
- የልጅ እንክብካቤ ሰጪ ስም እና አድራሻ (የሚመለከትዎ ከሆነ)
- በልጁ/በልጅቱ ግላዊ ሁኔታ ላይ የተመሠረተ የትምህርት ፕሮግራም/Individualized Education Program (IEP)፣ የሞግዚትነት/በማደጎ የማሳደግ የተንከባካቢነት ማረጋገጫ (የሚመለከትዎ ከሆነ)
- የልጁ-የልጅቱ ሶሻል ሰኩሪቲ ካርድ የሚያስፈልገው ለ (Maryland Children's Health Program (MCHP) የሚያመለክቱ ከሆነ ብቻ ነው